በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ታቦት - ክፍል ፩

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ታህሳስ ፯ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.



# ታቦት

- ቃሉ የግዕዝ ነው፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ 135 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡
- በኮፕት/በግብፅ ቴባ፣ በዕብራይስጥ ቴቦ/ቲቡታ፣ በዐረብ ታቡት ይባላል፡፡ በግዕዝ ግን ታቦት ይባላል፡፡
- ታቦት ማለት፡- የእግዚአብሔር ክብር መገለጫ የእግዚአብሔር የክብር ዙፋን ማለት ነው፡፡

- እግዚአብሔር አምላክ በታቦቱ ላይ ሆኖ ሙሴን እንደሚያነጋግረው ራሱ ስለነገረውና በታቦቱም ላይ ሆኖ ስላነጋገረው ነው የክብር መገለጫው የተባለው፡፡
- “በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ የእስራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ፥ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል፥ በስርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እነጋገርሃለሁ፡፡” *ዘጸአ 25፡22፡፡*
- “ሙሴም ወደ መገናኛው ድንኳን እርሱን ለመነጋገር በገባ ጊዜ በምስክሩ ታቦት ላይ ካለው ከስርየት መክደኛ በላይ ከኪሩቤልም መካከል ድምፁ ሲናገረው ይሰማ ነበር እርሱም ይናገረው ነበር፡፡፡፡” *ዘኁ 7፡89፡፡*
- ታቦት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመኖሩ ምልክት ነው፡፡
- ታቦት ለመጀመሪያ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሠራው ከግራር እንጨት ነው፡፡ “ከግራር እንጨትም ታቦትን ይሥሩ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፥ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን፡፡” *ዘጸአ 25፡10፡፡*
- ታቦቱም በውስጥና በውጭ በወርቅ እንዲለበጥ እግዚአብሔር አዟል፡፡ *ዘጸአ 25፡11፡፡* ሙሴም እንደታዘዘው አድርጓል፡፡ *ዘጸአ 37፡1-3፡፡*
- ታቦቱንና በታቦቱ ዙሪያ ያሉትን ንዋያተ ቅዱሳት እንዲሠራ የተፈቀደለትና የሠራ፣ እግዚአብሔር የመንፈስ ብልሃትንና ጥበብን ዕውቀትንና ማስተዋልን ሁሉ የሰጠው እግዚአብሔር ራሱ የመረጠው ባስልኤል ነበር፡፡ “ባስልኤልም ከግራር እንጨት ታቦቱን ሠራ ርዝመቱም ሁለት ክንድ ተኩል፥ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፥ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ነበረ፡፡” *ዘጸአ 37፡1-17፡፡*

# ታቦት…

- በታቦቱ ውስጥ አሥርቱ ቃላት የተፃፉባቸው ሁለት ጽላቶች ነበሩ። "እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው ጽላቱን ወስዶ በታቦቱ ውስጥ አኖረው፥ መሎጊያዎቹን በታቦቱ ዘንድ አደረገ፥ የስርየት መክደኛውንም በታቦቱ ላይ አኖረው።" *ዘጸአ 40:20።*
- ጽላት ማለት ቅዱስ ቃሉ የተጻፈበት ቅዱስ የድንጋይ ሰሌዳ ማለት ነው።
- ሁለቱ ጽላቶች ሙሴ በመጀመሪያ በሲና ተራራ 40 ቀንና 40 ሌሊት ንጹሕ ውሃ ሳይቀምስ ከጾመ በኋላ ከእግዚአብሔር እጅ የተቀበላቸው ናቸው። *ዘጸአ 33:15-22።*
- እስራኤል ሙሴ ከሲና ተራራ እስኪመለስ 40 ቀን መታገስ አቅቶአቸው አሮንን አስገድደው ጣዖት ሠርተው ሲሰግዱ አገኛቸው። በዚህ ጊዜ ለአምላኩ ቀናኢ ነውና ጣዖትን በማምለካቸው እጅግ ስለተናደደ ሁለቱንም ጽላቶች ሰባበራቸው።
- "እንዲህም ሆነ ወደ ሰፈሩ ሲቀርብ ጥጃውንም ዘፈኑንም አየ የሙሴም ቍጣ ተቃጠለ፥ ጽላቶቹንም ከእጁ ጥሎ ከተራራው በታች ሰበራቸው።" *ዘጸአ 32:19።*
- ቸርና መሐሪ የሆነ እግዚአብሔር ሙሴን ካጽናና ካረጋጋ በኋላ የሠበርካቸውን አስመስለህ አንተ ራስህ ሥራ እኔም እባርክልሃለሁ አለው። ሙሴም እንደታዘዘው አስመስሎ ሠራና እግዚአብሔር ባረከለት። ሙሴ ራሱ የሠራቸውን ሁለቱንም ጽላቶች እንደታዘዘ በታቦቱ ውስጥ አስገባቸው።
- "እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፦ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች እንደ ፊተኞች አድርገህ ጥረብ በሰበርኻቸው በፊተኞቹ ጽላቶች የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ። ነገም የተዘጋጀህ ሁን፥ በማለዳም ወደ ሲና ተራራ ወጥተህ በዚያ በተራራው ራስ ላይ በፊቴ ቁም። ከአንተም ጋር ማንም ሰው አይውጣ፥ በተራራውም ሁሉ ማንም አይታይ መንጎችና ከብቶችም በዚያ ተራራ ፊት አይሰማሩ። ሙሴም እንደ ፊተኞቹ አድርጎ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠረበ በነጋውም ማልዶ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወደ ሲና ተራራ ወጣ፥ ሁለቱንም የድንጋይ ጽላቶች በእጁ ወሰደ፥ እግዚአብሔርም በደመናው ውስጥ ወረደ፥ በዚያም ከእርሱ ጋር ቆመ፥ የእግዚአብሔርንም ስም አወጀ። …

# ታቦት…

- “… እግዚአብሔርም በፊቱ አልፎ። እግዚአብሔር፥ እግዚአብሔር መሐሪ፥ ሞገስ ያለው፥ ታጋሽም፥ ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት፥ እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ፥ አበሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል፥ በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ፥ የአባቶችንም ኃጢአት በልጆች እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድም በልጅ ልጆች የሚያመጣ አምላክ ነው ሲል አወጀ። ሙሴም ፈጥኖ ወደ መሬት ተጐነበሰና ሰገደ። አቤቱ በፊትህስ ሞገስን አግኝቼ እንደ ሆነ፥ ይህ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነውና ጌታዬ በመካከላችን ይሂድ ጠማማነታችንንና ኃጢአታችንንም ይቅር በለን፥ ለርስትህም ተቀበለን አለ። እርሱም አለው፦ እነሆ እኔ ቃል ኪዳን አደርጋለሁ በምድር ሁሉ፥ በአሕዛብም ሁሉ ዘንድ እንደ እርሱ ያለ ከቶ ያልተደረገውን ተአምራት በሕዝብህ ሁሉ ፊት አደርጋለሁ እኔም በአንተ ዘንድ የምሠራው ነገር የሚያስፈራ ነውና አንተ ያለህበት ይህ ሕዝብ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሥራ ያያል።” *ዘጸአ 34፡1-10፣ ዘጸአ 40፡20።*

- ይህም ታቦት በሙሴ ድንኳን ውስጥ ተቀምጦ፣ እግዚአብሔር አምላክ በዚያ ክብሩን እየገለጠ፣ እስራኤልም በድንኳኑ ደጃፍ በታቦቱ ፊት ለፊት ለእግዚአብሔር ስም እየሰገዱ፣ እግዚአብሔርን እያመለኩ፣ ለስሙ እየዘመሩ፣ የአምልኮ ሥርዓታቸውን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ቀጥለው በሕይወታቸው በደስታና በሰላም ይኖሩ ነበር።

- ሙሴ አርፎ ኢያሱ እስራኤልን ለመምራት ተተካ። በምድረበዳ እስራኤልን እየመራ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዝ ድንገት የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶበት ግማሽ ሚሊዮን እስራኤልን የሚያሻግርበት ድልድይ አጣ። ኢያሱም ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፣ ካህናት የቃልኪዳኑን ታቦት ተሸክመው ይሂዱና የሞላውን የዮርዳኖስን ወንዝ ይርገጡት፣ ወንዙም ለሁለት ይከፈላል፣ መሐሉም ይደርቃል እስራኤልም በሰላም ይሻገራሉ፣ ነገር ግን ሕዝቡ ጨርሰው እስኪሻገሩ ድረስ ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት ከወንዙ እንዳይወጡ፣ በመጨረሻም ይውጡ አለው።
- ኢያሱም እንደተባለው አደረገ። በታቦቱም አማካኝነት እግዚአብሔር አምላክ የሞላውን የዮርዳኖስን ወንዝ ከፍሎ አሻገራቸው ታቦቱ የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫ ነውና። *ኢያሱ 3፡1- ፍጻሜ።*

# <u>ታቦት…</u>

- ኢያሱ እስራኤልን እየመራ ኢያሪኮ ከነዓን ወይም ኢየሩሳሌም ደረሰ፡፡ ነገር ግን አሕዛብ የከነዓንን የኢያሪኮንና የኢየሩሳሌምን ዙሪያ ጥሩ በሆነ ግንብ አጥረው በሩን አንድ ብቻ አድርገው በከባድ ኃይል በሩን እያስጠበቁ ይኖሩበት ነበር፡፡
- እስራኤልም መግቢያ ስላጡ የእስራኤል መሪ ኢያሱ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፡፡ እግዚአብሔርም ሰማውና እንደተለመደው ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ቀንደመለከት ይዘው እየነፉ ስድስት ቀን ይዙሩት በሰባተኛውም ቀን ይፈርሳል አለው፡፡ እንደተባለውም አደረገ፤ የኢአሪኮም ግንብ እንደ እንቧይ ካብ እንደ ክረምት ገደል ተናደ፡፡ <u>*ኢያሱ 6፡1-22፡፡*</u>
- ኢያሱም ሰልፈኞቹን ይዞ ገባ፣ ጠላትን ሁሉ ወረሰ፣ ከነዓንን ለእስራኤል ርስት አድርጎ አካፈለ፣ ጋለሞታይቱ ረዓብም ከሞት የዳነችው በዚህ ጊዜ ነበር፡፡ <u>*ዕብ 11፡31፡*</u>
- ይህ ታቦት ዩየርዳኖስን ወንዝ ከፈለ፣ የኢያሪኮን ግንብ አፈረሰ፣ እግዚአብሔርም የኃይሉ መገለጫ አደረገው፡፡
- እግዚአብሔር አምላክ ክብሩንና ኃይሉን በታቦቱ ላይ እየገለጠ፣ እስራኤልን እንደ ባልንጀራ እያነጋገረ ከእስራኤል ጋር አድሮ ይኖር ነበር፡፡
- በዘመነ መሳፍንትም ካህናቱም ሆኑ እስራኤል በደሉ፣ በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን በጠላትነት ተነስተው ብዙ እስራኤላውያንን ፈጁ ካህናቱንም ገደሉ፡፡ ታቦቱንም ማርከው ወሰዱ፣ ወስደውም ከንቀታቸው የተነሳ አምላካችን ብለው ከሚጠሩት ዳጎን ከሚባል ጣዖታቸው ሥር አስቀመጡት፡፡
- ነገር ግን በታቦቱ ውስጥ የነበረው የእግዚአብሔር ኃይል የፍልስጥኤማውያንን ጣዖት አንኮታኮተው፣ እጅ እግሩን ቆራረጠው፡፡ ይህም በተደጋጋሚ ሦስት ጊዜ ሆነ፡፡
- በተጨማሪም በታቦቱ ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር ኃይል በፍልስጥኤማውያን ላይ ተደራራቢ መቅሰፍትን ለቀቀባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ፍልስጥኤማውያን ሳይየወዱ በግድ ታቦቱን ወደአገሩ ወደ ኢየሩሳሌም መለሱ፡፡ <u>*1ኛ ሳሙ 5፡1-ፍጻሜ ፡፡*</u>

# ታቦት…

- ***ታቦቱ ወደ አገሩ ሲመለስ ዳዊትና ሕዝቡ ሁሉ በእልልታና በሆታ ተቀበሉት፡፡*** "ዳዊትም ወዳዘጋጀለት ስፍራ የእግዚአብሔርን ታቦት ያመጣ ዘንድ እስራኤልን ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ሰበሰበ፡፡" *ቀዳ ዜና 15፡3፡፡*
  ***በዚህ ጊዜ አንድ ዖዛ የተባለ እስራኤላዊ ክህነት ሳይኖረውና ሳይፈቀድለት በድፍረት ታቦቱን በመንካቱ ወዲያውኑ ተቀሰፈ፡፡*** *2ኛ ሳሙ 6፡6-9፡፡*
- ***በእግዚአብሔር ስም የተጠራውን እግዚአብሔር ያከበረውን ሁሉ እንጨት ነው፣ ድንጋይ ነው፣ ሥዕል ነው ብለን መናቅና ማቃለል እንደሌለብንም ከዚህ እንረዳለን፡፡***
- ***ሕዝበ እስራኤል ታቦቱን ለማክበር ሲሉ ካህናቱ ተሸክመው ሲሄዱ ከታቦቱ ሁለት ሺህ ያህል ክንድ ይርቁ ነበር፡፡*** "በእናንተና በታቦቱ መካከል ያለው ርቀት በስፍር ሁለት ሺህ ክንድ ያህል ይሁን በዚህ መንገድ በፊት አልሄዳችሁበትምና የምትሄዱበትን መንገድ እንድታውቁ ወደ ታቦቱ አትቅረቡ ብለው አዘዙ፡፡" *ኢያሱ 3፡4፡፡* ***ዛሬም ምዕመናን ለእግዚአብሔር ክብር ሲሉ ከታቦቱ ራቅ ይበሉ የሚባለው ከዚህ የተነሳ ነው፡፡***

- ***ንጉሥ ሰሎሞን ታላቁን ቤተመቅደስ ሲሰራ ታቦቱን በታላቁ ቤተመቅደስ ውስጥ በክብር አስቀምጦታል፡፡*** "ካህናቱም የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦት በቤቱ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ከኪሩቤል ክንፍ በታች ወደ ነበረው ወደ ስፍራው አመጡት፡፡… ካህናቱም ከመቅደሱ በመጡ ጊዜ ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት ሞላው፡፡ የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶ ነበርና ካህናቱ ከደመናው የተነሣ ለማገልገል ይቆሙ ዘንድ አልቻሉም፡፡" *1ኛ ነገ 8፡6-11፡፡*

- ***ከዚያም አገልግሎቱን ቀጥሏል፡፡ የዚህ ታቦት ክብር በሐዲስ ኪዳን በሰማይ ታይቷል፡፡*** "በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ፡፡" *ራዕይ 11፡19፡፡*

ይቀጥላል…

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።